# ተነግሮ ከማያልቀው
# የፓልቶኩ ንጉሣች ጉድ
# ጥቂቱ !!

ንጉሥ ስንል ሀገርና ሕዝብን የሚመራ ብቻ አድርገን እናይ ይሆናል ፤ ዳሩ ግን ሀገርና ሕዝብን ከሚመራው ንጉሥ በተቀራረበ መልኩም ባይሆን እንኳ ፤ የፈላጭ ቆራጭ ሥልጣን ያላቸው ንጉሣች በፓልቶኩም ውስጥ እንደ አሸን እየፈሉ መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባል ። አንድ ግለሰብ የፓልቶክ መነጋገሪያውን ሩም ይከፍታል ፤ የሚያውቃቸው ጓደኞቹን ወይም አዲስ የተዋወቃቸውን የሩሙ መሪ አድርጎ ይሾማል ፤ በቀጥር የሚሠሩትንም ጭምር ማለት ነው ። ታሪክም-አፈታሪክም-ተረትም ይሁን ቀልድ ከሙዚቃ ጋር እነሆ ይባላል ። እንደ ኢትዮ ላቭም ከውስጥ ልብስ ሥር ያሉ ......... ሳይቀሩ ፤ በሳይንሳዊው ወይም በኢ-ሳይንሳዊ የዘፈቀደ አነጋገር ተተንትነው ይቀር ባሉ ፤ ነገሩ ሠለጠንን እንደማለት ይሁን እንጂ እንዳልተሠለጠነ ፤ ወይም የሥልጣኔው ደጃፍ እንዳልተረገጠ ይገባናል !! ወዘተ.......ፖለቲካውን ያለ ዕውቀትና ችሎታቸው በዘፈቀደ ከሚያቦኩት ጭምር በፓልቶክ ውስጥ የማይባል ነገር የለም ። የብዙዎቹ ፓልቶኮች ውይይት የሚቋጨው ሰማንያ ፐርሰንቱ በመከፋፈል ፤ በመናቆር ፤ በመሰዳደብ ፤ በመናናቅ ፤ አንዱ የሌላውን ምክርና አስተያየት በማጣጣል ብቻ ነው ። ወደድንም ጠላን በዚህ ሂደት ኢትዮጵያዊያን ታላቅ ትዝብት ላይ የወደቅን ፤ ወይም ግምት ውስጥ መግባታችን እንዳልተሰማን ነው የገባኝ ።

የፓልቶኩ መወያያ መድረክ ተጀምሮ ከ6/7 ወር በኋላ ነው ብቅ ብዬ ተሳታፊ መሆን የጀመርሁት ። እንዲያው በቀላሉ የመጀመሪያ ሰው ነኝ ማለት እችላለሁ ። ካለኝ ጊዜ አኳያ ጠንካራ ተሳታፊ ባልሆን እንኳ ፤ ለዚያች በናፍቆት ለምታንሰፈስፈን ኢትዮጵያችን በሚደረግ ትግል ላይ የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ ። ብዙዎቻችን በዓይኖቻችን ሳንተያይ ፤ ማንነታችን ላይ ዕውቀናን ሳንጨብጥ ፤ ግን በሀገራችን ጉዳይ ላይ እንድንወያይ ያደረገን ዋናው ቋንቋችን ነው ። በአንዳንድ አጋጣሚ ስብሰባዎች ፤ ወይም የተቃውሞ ሰልፍ ላይ በአካል ተያይተንም ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያበረከትናቸው በጎ ተግባራትም ማንነታችንን አጉልቶ ማሳየቱም ግልጽ ነው ።

ደርግ በመጣ ማግሥት የነጠፈብን አኩሪው ግብረ-ገባዊ ሥርዓታችን በዚህ ጋጠ-ወጦች በበዙበት ወቅት ያለመገኘቱ በእጅጉ ጎድቶናል !! ታላቅ ተመክሮ ያላቸውና ሕዝብ ሊያስተምሩ ፤ መልካም አቀጣጫ ሊየሲዙ የሚችሉ በዕድሜ የበለጸጉ ሰዎች በተለያዩ ፓልቶኮች ውስጥ እንደ ኢትዮጵያዊነታቸው ለመሳተፍ መጥተው ሲዘረጠጡና ሲሰደቡም ሰምቻለሁ ። “ ያንተ ዕድሜ አልፎአል !! የድሮ ፖለቲካ አሁን አይሠራም !! የኛን ሕይወት እኛ ልንመራው ይገባልና ከነሽበትህ ተከብረህ ተቀመጥ !!! “ የሚል ኃይለ-ቃል የተወረወረባቸው ሰዎች እንደነበሩ በሃዘን ነው የማስታውስ !! በርግጥ ያንን የውርደት ቃል ሰምተው ዳግመኛ ፓልቶክ ውስጥ ላይመለሱበት ፤ ተስፋ ቆርጠው የቀሩትን እኔ እንኳ በግሌ የተወሰኑ ሰዎችን አውቃለሁ ። ይህንን ንጉሣቹም ያውቃሉ ! በተረፈ ቤት ይቁጠረው !!!

ከኢትዮጵያዊያን የማይጠበቅ ጠያፍ ቃላት በመወናጨፍ ፤ በዚህም ትልቅ ደስታ የሚጭርላቸው እንዳሉ ለማወቅ የሚፈልግ ካለ ኢትዮ-ላቭ ገብቶ ማድመጥ ይችላል ። ኢትዮ ላቭ በዋናነት ይቀመጥ እንጂ ያንን ፈለግ ተከትለው ጠያፉን ቃላት የሚወናጨፉም ብዙ ሩሞች አሉ ። “ ኢትዮ-ላቭ ፎር ኦል እንደ መጠሪያው ያማረ ሳይሆን የጋጠ-ወጦች መሰባሰቢያ ነው !! “ የሚሉም ብዙዎች ናቸው ። እኔም እንደ መጠሪያው መስሎኝ ከገባሁ በኋላ ነገሩ ስላልጣመኝ ፤ ፈትለክ ብዬ መውጣቴን አስታውሳለሁ ። ሌሎች እንደሚሉትም ነገሩ ዕውነት ሆነና ከአምስት ደቂቃ በላይ ሳልቆይ ሩሙን ለቀቄ ዳግመኛ ሳልገባበት እስካሁን አለሁ ። ዛሬ በግላጭ የመጣው ባኅልና ዕምነታችን ላይ ያነጣጠረው የአጥፊ ኃይላት መርዝ ፤ በዘመነ ኃይለ ሥላሴም የወጣቱን ትውልድ አዕምሮ ለማላሸቅ በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ ገብቶ ነበር ፤ ሆኖም በዚያን ጊዜ የነበረው ትውልድ በቀላሉ እጁን ስላልሰጠ ፤ ሀገራችንም መንግሥት ስለነበራት የተቻለውን ያህል ለመከላከል ተሞክሯል ።

የኢትዮጵያን ሕልውና የሚፈታተኑ ኃይላት የሀገራችንን ማንነት ለማጥፋት በተለያየ አቅጣጫ እየተዋጉን ባሉበት በአሁኑ ወቅት ፓልቶኩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጎላቸዋል ። ውጊያው እየተከወነ ያለው ከቀንደኛ ጠላቶቻችን ጋር ብቻ ሳይሆን ፤ ቋንቋችንን ፤ ባኅላችንን ፤ ማንነታችንን ጠንቀቀው ከሚያውቁ በውክልና ከሚሠሩ ከኛም ሰዎች ጋር ነው ። እነዚህ የኛ የምንላቸው ሰዎች ጥንትም አያት አባቶቻቸው ባንዳ የነበሩ ፤ የባንዳ ልጆች ባንዳዎች ናቸው ። በባንዳነት ውርስ ተልዕኮ ሌላውም የኩሩ ኢትዮጵያዊ ልጅ የአያት አባቱን ዓርማ ከሜዳ ላይ ጥሎ ፤ በተንኮለኞች ሤራ ተተብትቦ ከሀገርና ወገን ይልቅ ሆዱን አስበልጦ የተረጋጋች ኢትዮጵያ እንዳትፈጠር ታላቅ መሰናክል መሆኑ ታሪካዊ ሐቅ ነው ። እንዲያው በለስ ባይቀናን እንጂ ከሀገር አጥፊዎቹ ይልቅ ሀገር ወዳዶቹ በርካታ ነበርንኮ ፤ ይህችን ሀገር ለማዳን ጊዜ የማይወስድብንም ነበርንኮ ፤ ግን በውዥንብር ተሞልተንና ቀናው አቅጣጫ ስለጠፋብን ፤ ቀናውንም አቅጣጫ የሚያሳየን የኢትዮጵያ ትንሣኤ ራዕይ ያለው መሪም ብቅ ባለማለቱ አሁንም በዚያው ውዥንብር ውስጥ እየዳከርን እንገኛለን ።

ዶክተር ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል እንደሚባለው ሁሉ ፤ አንድ ወቀት በጠና ለታመሙ ግለሰብ መድኃኒት አዋቂ ይፈለግና አዋቂው መጥተው ምርመራ ካደረጉ በኋላ ፤ “ ለዚህ ህመም አህያ መታረድ አለበት ፤ ሰውየው የሚድኑት በአህያው ሥጋና ደም ነው ። “ ብለው ሊደረግ የሚገባውን ነግረው ይሰናበታሉ ። ሌላው አዋቂ መጥተው የቀድሞውን አዋቂ አስተያየት ነቀፈው የግል ችሎታቸውን ሲያሰሙ የታረደውን አህያ ይጥላሉ ። ሰውየው አልዳኑም ፤ አሁንም ሌላ አዋቂ መጥቶ የመጀመሪያውን አዋቂ በመደገፍ ፤ መድኃኒቱ የአህያ ሥጋና ደም ነው ብሎ ሲገልጽ ፤ የጣሉትን አህያ ፍለጋ ተሂዶ ግን አህያው ምኑም ሳይገኝ ቀርቶ ታማሚውም ሞቱ ይባላል ። በአባባል ሲገለጽ ፤- “ ይሆናል ብለው አህያ አረዱ አይሆንም ብለው ጣሉ ፤ እንደገና ይሆናል ብለው ሲፈልጉ አጡት “

ይባላል ፡፡ ከአጥፊዎቹ ጋር የገጠምነው ትንቅንቅ አልተቋረጠምና ክቡር ባኅላችን እየተወጋ ነው ፡፡ የምንፋቀርበትና
የምንከባበርበት የክርስትናውና የሙስሊሙ ሃይማኖታችን እየተወጋ ነው ፡፡  የረጅም ዘመናት ታሪካችን እየተወጋ
ነው  ፡፡ በኢንተርናሽናል ደረጃ ዕውቅና ያለውን ፊደላችንን ፤ ቋንቋችንን ፤ በጥቀሉ የኛ የምንለውን ሁሉ  በፓል
ቶኩ  ግዛታቸው ጥቃት እያካሄዱበት ነው ፡፡  በከፋፍለህ  ግዛው የተካኑ ኃይላትና ቡችሎቹ ያለ  ምንም  ዕረፍት
መዋዕለ-ነዋያቸውን እየረጩ ለሆዳሞቹ ጠንካራ ሞራል እየሰጡና ፤  የኛን ሞራልና ትግላችንን እያዳከሙ ፤  ሀገሬ
ብለን  የምንጮህበትን አንደበት ለመዝጋት ደፋ ቀና እያሉ ነው ፡፡  በቅርቡ ለሙስሊምና-ክርስቲያን  መፍትሔ
ለማግኘት በሚል የፓልቶክ  መርዝ መርጪ ክፍል ተከፍቶ ሕዝቡን  ሲያናክሱ እንደነበረና ፤  አሁንም በማናከስ
ላይ እንደሚገኙ ግልጽ ነው ፡፡ ባለፋት ወራት ውስጥ ደግሞ በአላሙዲን ሰም የተሰየመ አንድ ሩም ተከፍቶ እንደ
ነበረና ወዲያው አንደተዘጋ አስታውሳለሁ ፡፡ “ ጅብ በቀደደው ውሻ ይገባል “ ይባል የለ ? ጨቀላ ወጣት ሴቶች
ልጃገረዶችን ወዘተ..ዓረብ ሀገር ሥራ አለ በሚል ፤ በእጅ-አዙር ባሪያ ሽያጭ እየላኩ ፤  የዓረብ ሴቶች በሚያደ
ርሱባቸው አደጋ ብዙዎች የሞትና የአካለ-ጎዶለነት ችግር እንደገጠማቸው ሁሉ ፤  አሁን ደግሞ  “ ሸንጥና ዳሌ
ሲወያዩ.......... !!  “ ሞዴል ለመሆን  የምትፈልጉ አንረዳችኋለን የሚል ዓላማ ይዞ ነበር የተነሳው ፡፡  ባጠቃላይ
የተዋለብን ግፍና ደባው ከምን መጣ ብለን መጠየቅ ሳያስፈልግ ፤ ወያኔንና ሻዕቢያን በመኮነናቸውና በመስደባቸው
ብቻ ኢትዮጵያዊ መስለው በጓሮ በር ግን መረጃ በሚያነጥፉ  የኢትዮጵያዊያንን ትግል በማዳከም ላይ በሚገኙ
የፓልቶኩ ቀጥረኞች ነው ፡፡  እነዚህ የተፈጥሮም ሆነ  የሚዲያ ሕግ የማይገዛቸው ዘላኖች ጉዳቸው ብዙ ስለሆነ ፤
ለኢትዮጵያም  ሆነ ለሕዝቦቿ አንዳች የትግል  ፍሬ  ስለማያስገኙ ተጠንቀቀ ሐበሻ ከማለት በቀር ሌላ የምለው
የለኝም ፡፡ ጠላቶቻችን አንድ ሆነው በኅብረት የሚፈጽሙብን ሤራ እየጠነከረ ፤ እኛ ግን ኅብረት አጥተን ጥቃቱን
መከላከል ያለመቻላችን  ምን ያህል ሕዝባችንን እንደጎዳው ፤ ሀገራችን የባዕዳን መጠቀሚያና ፤ የኛን ረሃብ አስተ
ናጋጅነት ለዓለም ማሳየቷ ሊሰማን ይገባል  ፡፡ ስለዚህም ይህን ሀገር በታኝና ዓይን ያወጣ ጥቃት ለአንዴና ለመ
ጨረሻ ጊዜ በጥንካሬ መከላከል ይኖርብናል ፡፡

የፓልቶኩ ዘላን ንጉሦች ሌላውን ሰው መስደብ ፤ ማዋረድ ፤  መብቱንም  መንካት ለነሱ ግን የተፈቀደ መብት
አድርገው ነው የሚመለከቱት ፡፡ ወያኔ የሕዝቡን ድምጽ ያፈነ ዲክታተር ነው እያሉ በየፓልቶኩ ይጮኹ እንጂ ፤
እነሱ በሰለጠነው ዓለም ውስጥ ተቀምጠው ምን እያደረጉ ነው ያሉት ? በፓልቶክ ውስጥ ሕዝቡ የፈለገውን እንዳ
ይናገር ፤ ሃሳቡን በነፃ እንዳይገልጽ አንደበቱን እየዘጉ አይደለምን ? “ የፈለገውን እንበል እኛን አትናገሩን ፤ ቀዩን
ጦርና የባውንስ አጥቂ መሣሪያችንን ለቀንባችሁ ዘላለማዊ ጸጥታን እናጎናጽፋችኋለን “ እያሉ ይዝታሉ ፡፡ መዛት
ብቻም ሳይሆን ያንን አዳፍኔያቸውን እየላኩ ለናንተ እኩይ አስተሳሰብ  አልገዛም  የሚለውን ወገን ያሰቃዩታል ፡፡
ስለ  ሀገሩም ሆነ ስለተጣሰበት መብቱ  መተንፈስ አይችልም ፡፡  አንዳንድ ታዳሚዎችም  የመዋጮ ጉዳይ ተነስቶ
ሲወያዩ  ፤  “  የገንዘብ  መዋጮ በየጊዜው አውጥተናል ፤  ግን የሥራችሁን ፍሬ ማየት አልቻልንም ፡፡  የገንዘብ
አያያዝ ዘዴና ተጠያቂነትም ያንሳችኋል ፡፡  “ ስላሉ ብቻ በቀይ ካርድና በባውንስ የተቀጡ በርካታ ሰዎች እንደነ
በሩም አስታውሳለሁ ፡፡ ብቻ ነገሩ ይገርማል !! ታዳሚውም  የዋዛ አይደለም ፤ ወዲያው ስሙን ቀይሮ ይመጣና
ሃሳቡን በሌላ መልክ ለማስረዳት ይሞክራል ፤ ካልሆነም አድሚኑን አዋርዶ ይወጣል ፡፡  ይህ ውኸንብር  ወይም
ውዝግቡ እንደቀጠለ ነው ፡፡  ፓልቶኩ በሰከነ ሁኔታ  የሀገርን ጉዳይ የሚወያዩበት ፤  ማለትም ፖለቲካውን ማኅበ
ራዊ  ሕይወቱን ፤ ኢኮኖሚውን ባካተተ የሚወያዩበት ፤  የአዋቂዎችን ምክር የሚቀበሉበትና መፍትሔ የሚፈጠ
ርበት ሳይሆን ፤ ስድብ ክርክር ጭቅጭቅ  የሚወናጨፉበት ፤ ትውልዱንም የቁም ነገር ባለቤት እንዳይሆን የሚደ
ረግበት ሀገር በታኝና አጥፊ ፕሮፓጋንዳ የሚነዛበት ፤  ከአዕምሮ አደንዛዥ ዕጽ ባልተናነሰ መልኩ ፤  የትውልዱን
አዕምሮ ማላሸቂያ ነው ፡፡  ከኛ ከኢትዮጵያዊያን ጋር የፓልቶኩን ነገር ብናስተያየው ፤ ፓልቶኩ የሠለጠነ ሆኖ
ነገር ግን ያልሠለጠኑ ወይም ሊሠለጥኑ ያልፈለጉ ተጠቃሚዎችን ነው ያጋጠመው ፡፡  ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ራስ
እንጂ ጭራ አይደለችም !!   ጨዋነት -ደግነት-አልደፈር ባይነትም የተፈጥሮ ሀብታችን ነው ፡፡  ያንን እንደ አባት
አያቶቻችን- ወይም ቀድመ አያቶቻችን አጥብቀን ባለመያዛችን ሠለጠንን እያልን ደነቀርን !!  አብዛኛው ሩም
በሀገር አጥፊው ወያኔ የሚመራ ነው ተብሎ ከተነገረም ቆይቷል ፡፡ ታዲያ በስሜት ተገፋፍቶ በየሩሙ ከመሮጥና
በፓልቶኩ ንጉሦች ከመቀጣት ይልቅ ፤  ይህንን መጥፎ አዝማሚያ መዋጋት ያለበት ይህ ትውልድ ራሱ  መሆን
አልነበረበትምን ? ሀገሬን እወዳለሁ ሕዝቤን አድናለሁ የሚለው ይህ ትውልድ  እስከ መቼ የፓልቶኩን ንጉሦች
በዝምታ ይመለከታል ? ለምንድነው ከወያኔ ተንኮል ነፃ  የሆነ የአዲሱ ወጣት ትውልድ ሩም ከፍቶ አርቲ-ቡር
ቲዎችን የማይዋጋው ?  ይህ የኔ ጥያቄ  ምናልባት በቀጣዩም ትውልድ ያስጠይቅ ይሆናልና ከልብ ቢታሰብበት
መልካም ነው !! ለማንኛውም ነገሬን አልቋጨሁም

## ማምታታት ወይስ ግንዛቤ ማጣት ?

አሁን ከሚታየው አዝማሚያ ሩም መክፈትና የፓልቶክ ንጉሥ መሆን ቀላል ነው ፡፡  በሌላ መልኩም ቀላል
ላይሆን ይችላል ፡፡  ማለትም  ንጉሥ መሆን የሚፈልገውን ሰው ጥንካሬም ይጠይቃልና ነው ፡፡  ለማንኛውም
በፓልቶክ ውስጥ የሚመጣው ንጉሥ  በራሱ ተነሳስቶ ወይም በቀጥር እንደመሆኑ  ከነዚያው ከጠላቶቻችን ጋር
እየዶለተ ፤ የታሪክ ራስ የሆነቸውን ሀገራችንን ፤ የታሪክ ጭራዎች እንዲያጠፏት ውክልናውን ለመከወን ይፍጨረ
ጨራል ፡፡ እኛም ኢትዮጵያ አትሞትም ብለን የሞት-ሽረት ትግላችን በተለያየ ሁኔታ እየቀጠለ ባለንበት በዚህ
ወቀት በርካታ የማምታታት ሥራዎች እየተከወኑ ለመሆኑም ፤  የሁላችን ልቦና ያውቀዋል ፡፡ ያም  የሚካሄደው
በአብዛኛው በፓልቶኮች ውስጥ ነው ፡፡  እስቲ ተዝታ ይጭርላችሁ እንደሆን ለአብነት ያህል በፓልቶኩ ከተከወ
ኑት ማምታታቶች ጥቂት ላስቀምጥ ፤

አንድ ወቀት በሀገራችን የኪነት ባለሙያዎች ፤   ወይም አርቲስቶች ላይ የዘነበው የጥላቻና የስድብ ዶፍ
ለከረንት አፌርስና ጥቂት ሩሞች ታሪከ-መዘክር ሆኗል ፡፡  ጥላቻውን ከመቀበሉ አኳያ ፤ አስቴር ፤ ማህሙድ ፤

ሰሎሞን ፣ ኤፍሬም በዋናነት የሚጠቀሱ ቢሆንም ፣ እንደ ሀገራችን አባባል አንድ ሰው መስመር ሲያልፍና ሲባልግ " ወጥ ረገጥህ !! " ይሉታልና ፣ ሰሎሞን እንኳ ወጥ ረግጦ ፣ ራሱን በራሱ ጠልፎ ጥሏልና ዋጋውን ነው ያገኘው ማለት ይበቃል ። ሰድቦ ለማሰደብ ፣ ጠልቶ ለማስጠላት በኛው በሀገር ልጆች መሃል ጥላቻን ለመፍጠር የተካሄደውና አሁንም እየተካሄደ ያለው ደባ ከየት መጣ ? ብለን የምንጠይቅ ከሆነ ፣ መልሱ አንድ ነው ፣ ከነ ዚያው ከአጥፊዎቻችን ጎራ መሆኑን አንጠራጠርም ። ካለፈው ሁኔታ ብናስታውስ ፣ አርቲስቶቹ ከወያኔ ጋር አብ ረዋል ፣ ከገዘፈው ሀገር አጥፊ ከአላሙዲን ጋር እጅና ጓንት ሆነዋል !! ሆዳም አርቲስቶች ናቸው !! በሚል ነው የጥላቻው መንስኤ ። ከዚህም ሂደት የተላለፈው ውሳኔ የሚያወጡትን ሙዚቃ ማንም እንዳይገዛ "ቦይኮት " እንዲደረግ የሚል እንደነበረ የቅርቡ ጊዜ ትዝታ ሸው ይለናል ። ምናልባት የፓልቶኩ ንጉሦች እንደ ወያኔ ዓይኔን ግንባር ያድርገው ካላሉ በቀር !! ለነገሩ የተቀዳው የድምጽ ዶኩመንት ስላለ ዓይኖቻቸው ግንባር ሆነው ይቀራሉ እንጂ ክህደቱ ፍሬ አልባ ነው የሚሆን ።

ታዲያ በቅርቡ ታዋቂ ሰዎችን ጠርቶ ማነጋገር በሚል ፕሮግራማቸው ሥር ፣ የከረንት አፌርስ ንጉሦች ታዋ ቂውን አርቲስት ማህሙድ አህመድን በመጋበዝ ዘውድ ቀረሽ ሙገሣ አድርገውለት ፣ ከአፍቃሪ ወያኔነት ይልቅ ዕውነተኛ የኢትዮጵያ ልጅነቱን አረጋግጠውለታል ። " በአንድ ራስ ሁለት ምላስ " እንዲሉ በሁለተኛው ምላሳ ቸው ያስተላለፉትን ዕውቀና እኔም እጋራዋለሁ ። ማህሙድ ከወጣትነት እስከዚህ ዕድሚው ፣ ለሀገርና ለሕዝቡ ያበረከተው አገልግሎት ከባድ በመሆኑ ፣ በበኩሌ ይገባዋል ነው የምለው ። ከዚሁ አንፃርሌሎቹም አርቲስቶች ሁለተኛው ምላስ እንደማይነፈ ጋቸው አልጠራጠርም ። ግን እንዲያው ለነገሩ ይህ በከረንት አፌርስ የተናፈሰው ጥላቻና ቦይኮት በትክክለኛ ማስረጃ በተደገፈና ፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሆን ተብሎ የተደረገ ሤራ ስላለ ነው ? ወይስ ሙያዊ ግዴታቸውን በመወጣት ከሙያቸው ውጤት ሊያገኙ የሚገባቸውን ጥቅም በመፈለጋቸው ? ይህ ነገር ተለይቶ መቀመጥ አለበት ። ከሙያቸው ውጤት ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ፣ ሀገርን በማጥፋት ሊያስጠይቃቸው የሚያስችል መሆን የለበትም ። ነገር ግን እናት ሀገራቸውን ለማጥፋት በስውርም ይሁን በግልጽ የተፈጸመ ሤራ ካለ ፣ ማስረጃው ለአደባባይ መቀረብ ይኖርበታል ። ይህ ጉዳይ ሚዛን ላይ የተቀመጠ ወይም በግንዛቤ ደረጃ የተፈረጀ ስለማይመስለኝ በሁለተኛው ምላሳችሁ የምትሉትን በሉና ያስቀየማችኋቸውን ወገኖቻችንን ይቅርታ ጠይቁ ፣ ወይም በማስረጃችሁ አሸናፊነታችሁን አረጋግጣችሁ ሀገርን በድለዋል የተባሉት አርቲስቶች የሚሉትን ይበሉ ። እንደ ሀገር ልጆች የምንተያይ ከሆነ !!! የሙያ ጉዳይ ከተነሳ ዘንድም ትንሽ የምለው ይኖረኛል ፦

በመሠረቱ አንድ ባለሙያ አገልግሎት የሚሰጠው ኃጥኡንና ፃድቁን በመምረጥ አይደለም ። አናጢው ለሙ ያዊ አገልግሎቱ ገንዘብ እስከተከፈለው ድረስ የአናጢ ሥራውን ለእገሌ በማይባል ልዩነት ይከውናል ። ባለታክ ሲው ወያኔ ነህ ብሎ አልጭንህም ማለት አይቻለውም ። ዶክተሩ ወያኔም ባይሆን ወያኔውን ማከሙ አይቀርም ። ነጋዴው ዕቃዩን ለወያኔዎች አልሸጥም ማለት አይቻለውም ፣ የመግዛት ወይም ያለመግዛት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ወዘተ...... ብዙ ነሮች ከወያኔ ጋር እየተካሄዱ ነበር ፣ ወደፊት ወያኔ ሥልጣን ላይ እስካለም ድረስ ሊካ ሄዱም ይችላሉ ። እኛ የትግሉ ስልት ሲያንሰን ጣታችንን ንጹሃን ግለሰቦች ላይ እንቀሥራለን እንጂ ፣ በዕውነተኛ መልኩ ብናየው ግን በአርቲስቶቻችን ላይ የተደረገው ጥላቻና ቦይኮት ፈጽሞ አግባብ አልነበረም ። አግባብ ባለ መሆኑም ነው ፣ በከረንት አፌርስ ውስጥ በማህሙድ ላይ የተላለፈውን የስድብና እርግማን ውርጅብኝ ሁሉ በሁለተኛው ምላሳቸው የሻሩት ። በከረንት አፌርስና በሌሎችም ሩሞች በሀገር አጥፊነት ወንጀል የተፈረጁት አርቲስቶቻችን በአንድ ዓይነት እንጂ ፣ በተለያዩ ወንጀሎች አልተጠየቁም ። ታዲያ ማህሙድ ነፃ ወጥቶ የሌ ሎቹን ነፃ ያለመውጣት ንጉሦቹ ምን ይላሉ ?

እኔ እንኳን እንደወጣሁ የቀረሁ ነኝ ! ወደ አገር ቤት ለመሄድ ዕድሉ የገጠማችሁ አላስተዋላችሁ እንደሆን እንጂ ፣ በሌሎቹ ባለሙያዎች ዘንድ ብዙ የሚባሉ ነገሮች አሉ ፣ እንደሰማሁት ከሆነ ፣

"የኔ ተወልደ ሐጎስ አንተ አባመስጠት !
አሻቀቦ የሚያይህ ጠላትህ ይታክት !!

እየተባለ የሚሞገሰው ወያኔና ብር ግንባሩ ላይ የሚለጠፍለት በጥንቱ አነጋገር "አዝማሪው " ወይም የክራርና የማሲንቆው ባለሙያ /አርቲስት/ አብረው በመኖር ላይ ናቸው። በነገራችን ላይ በዲክታተር መንግሥታት የሚመሩ ሀገራት ውስጥ የሶስት ዜግነት ቀርጽን የሚያመላክቱ ሕዝቦች ናቸው ያሉበት። 1/ በመሪው ጎሣ ሥር የተካተቱና ሥልጣነ መንግሥቱን የሚመሩ ፣ 2/ የመሳሰለ የጥቅም ግንኙነት ባይኖራቸው እንኳ በግላቸው ሠርተው የዕለት ኑሯቸውን አሸንፈው የሚኖሩ ፣ 3/ ፈጽሞ እንደ ዜጋ የማይታዩ ፣ ብትኖር ብትሞት ስላንተ አያገባንም ተብለው የተናቁ ፣ በረንዳ አዳሪና ኑሯቸው የጎዳና ሴተኛ አዳሪነት፣ እንዲሁም እሥር ቤትን ኑሯቸው ያደረጉ / ወመኔ / የሚባሉ የተበደሉ ዜጎች ናቸው ። ከላይ የተገለጸው ሥነ-ግጥም እንደሚያመለክተው ተወልደ ሐጎስ በአሁኑ ጊዜ በአንደኛ ደረጃ የሚታይ ዜጋ በመሆኑ ፣ እነዚህ 2ኛና3ኛ ዜጎች ከተወልደ ጋር ጥላቻ የላቸውም ማለት አንችልም ። ጥላቻው ገንፍሎ እስኪወጣ እንጂ !! 2ኛው ስንኝ ላይ አዝማሪው ምን አለ ? ብለን ብናስተውል ፣ " አሻቀቦ የሚያይህ ጠላትህ ይታክት !! " ነው ያለው ። ይህ ባለሙያ በ2ኛና3ኛ ደረጃ ዜግነት የተፈረጁና ፣ ተወልደ ሐጎስን አሻቀበው የሚያዩትን የራሱን ወገኖች እየረገመ !! ተወልደን እያስደሰተ የዕለት ኑሮውን ለማሸ ነፍ ይሞክራል ፣ የመኖር ነገር ነውና !! ። ሀገር አጥፊዎች ጋር ተባብረዋል የተባሉት አርቲስቶቻችን ግን ፣

"የኔማ መለሰ አብረቀራቂ ራስ !!
አላየሁም ጭራሽ ካንተ የሚደርስ "
አይርበኝ አይጠማኝ ችግር አይነካኝ
የኔን አላሙዲን ክፉ አይንካብኝ !!

ብለው አልዘመሩም ። ምናልባት ቀደም ሲል ዝና ያተረፉበትን ሙዚቃ ከጥሩ ውዝዋዜ ፣ ወይም ዳንስ ጋር
አስነክተው ሊሆን ይችላል በኔ ግምት ። ያም ሆነ ይህ እኛኮ ኢትዮጵያ ያፈራችን የአንዲት ሀገር ልጆች ነን ፣
አንዳችን ብናጠፋ ሌሎቻችን ጥፋት ከማራገብ በመካከላችን ይቀርታ እንዲመጣ ፣ በፍቅራችን መሃል ነፋስ እን
ዳይገባ ማድረግ ይኖርብናል የሚል ዕምነት ነው ያለኝ ። ለዚያም ነው የፓልቶክ ነገር አስፈሪ ነው ለማለት
ያነሳሳኝና ትግላችን ከመነተቱ የተነሳ ለችግሮቹ እልባት እንድናገኝለት የገፋፋኝ ።

ባለሙያዎቹ ሕይወት ከወያኔ ጋር እስካስተሳሰራቸው ድረስ አብረው ይኖራሉ ። ማለትም አንዱ ሲያሞግስ ሌላ
ውም ሲሞገስ ! ስለዚህ ትንሹን ነገር ወይም በቀላልና በዘዴ የሚፈታውን አክርረን እርስበርስ ተናቁረን የከረረው
እስኪበጠስ ድረስ የምናራግበው ሁኔታ ትክክል አይደለምና ሊቀጭ ይገባዋል ። የፓልቶኩ ንጉሦችም ለምን ተነ
ካን ? ለምን ሊስ ተሰነዘረብን ? ከማለት ይልቅ ፣ በየቤቱም የታፈነ ሌላም ብዙ ሊስ ወደፊት ስለሚመጣ ፣ በእ
ርግጠኛ ማስረጃ ለሚቀርብባችሁ ማንኛውም ደካማ ጎናችሁ ሊሶቹን ለመወጥ ዝግጅት አድርጋችሁ ፣ ለዚህ
ለሚያናክሰን አጉል ባኅሪ እልባት ልታገኙለት ይገባል ። ይህን ስህተት እየፈጸማችሁ ያላችሁት ዕውነተኛ ኢትዮጵ
ያዊያን ከሆናችሁ ማለቴ ነው ። ወያኔ ከሆነ ግን ሥራው ያጠፋዋልና እንጠብቃለን !! ያም የማይቀር ነው ።
ባለፉት ሳምንታት “ ማርገብ “ በሚል ርዕስ በኢትዮ-ሚዲያ ላይ ያቀረብሁትን ሥነ-ግጥም ብትመለከቱ ምናል
ባት ለዚህ እየተናቆርን ላለንበት ሁኔታ ጥቂት ያስታግሰን እንደሆን ብዬ ነውና ከልብ አስተውሉት ፦

አርቲስቶቻችን በተነቀፉበት ወቀት ፣ ከአንዳንድ ስሜታዊ ሰዎች በዚያን ጊዜ ያደመጥሁት እስከ ዛሬም ይገርመ
ኛል !! አንድ የከረንት አፌርስ ታዳሚ ነው ፣ በመጀመሪያ አገላለጹ አስቴር አወቀን በጣም እንደሚወዳት ካስ
ረዳ በኋላ ፣ “ ከወያኔ ጋር አብራለች መባሏን እንደ ሰማሁኝ ብዙ ዓመት ያጠራቀምሁትን የሷን ሲዲዎች ፣ የቴፕ
ካሴቶች ዱቄት አደረግኋቸው "ሲል አስደምጦናል ። በዚህ ስሜታዊ ሰው ያልተገረመ አልነበረም ። ምናልባትም
የሱን እርምጃ የወሰዱም ሌሎች ሊኖሩ ይችላሉ አላውቅም ። በበኩሌ ግን እዚያ ደረጃ አልደረስሁም ፣ ስለ
አርቲስቶቻችን ያደመጥሁት ሁኔታም አላሳመነኝም ፣ አሁንም አላምንም ። ከጥንት ጀምሮ የሸመትሁትን ካሴትም
ሆነ ሲዲ ወይም ዲቪዲ 1/ ገንዘቤን ስላወጣሁበት ፣ 2/ ሙዚቃዎቹ የኔ ብቻ ሳይሆኑ የሀገር ቀርስነታቸውን
ከመረዳት አኳያ ፣ 3/ የአርቲስቶቻችን ሥራዎች መከበር አለባቸው የሚል ፣ የራሴ ዕምነት ስለነበረኝ ጭምር
የብዙ አርቲስቶች ሥራዎች በኔ ዘንድ ተጠብቀው እየኖሩ ነው ።

ተጠቃሾቹ የሀገራችን አርቲስቶች ኢትዮጵያን ለማጥፋት በቀጥታ ከወያኔ ጋር አብረዋል ለማለት በቂ ማስረጃ
መጥቀስ ፣ / con-crete evidence/ ማቅረብ ያስፈልጋል ። ዕውነትን ሳይጨብጡ በስሜታዊነት ጋልቦ ፣ የሐቀኛ
ኢትዮጵያዊያንን ስም ማጥፋት ! የትም አያደርስም ። ዕንባዋ እንደ ጥላሁን ገሠሠ ሲመነጭላት ባላይም እንኳ ፣
ሀገሬ ሀገሬ ብላ ለቀሶ ቀረሽ ዘፈኗን የምታንቀረቁረዋ አስቴር አወቀ ፣ ዕውን እሷ ነች የእናት ሀገሯን ጥፋት ከወ
ያኔ ጋር የምትከውን ? ለመሆኑስ ከሙያ ሽያጭ ውጭ ሀገርን ሊያስጠፋ የሚያስችል ምን የተገኘ ማስረጃ አለ ?
ምናልባት በሁለተኛው ምላሳችሁ ይቀርታ ትጠይቋት እንደሆን እንጂ ፣ በበኩሌ እሷ የዚያ ሰው እንዳልሆነች
ይሰማኛል ። ማምታታት ወይስ ግንዛቤ ማጣት ያልሁትም ለዚያ ነው ። ምናልባት ንጉሦቹ ወደ ሰው ኅሊና
ትመለሱና ራሳችሁን ለዕውነት ታስገዙ እንደሆን ብዬ እንጂ !! አርቲስቶቻችን እናንተን ለመቃወም ቢፈልጉ ኃይሉም
ችሎታውም አንሷቸው አይደለም ፣ ምናልባት ለርካሽ ወሬ ቦታ ባለመስጠትና በንቀት ተመልክተዋችሁ ይሆናል
ዝምታን የተላበሱት እኔ እንጃ !

ባለፈው ዓመት እንኳ ቴዲ አፍሮ ሽራተን ውስኪውን እየጠጣ ይዝናናል !! ነዋይ ደበበ ከወያኔ ጋር ሳይስማማ
አልቀረም !! የሚሉ ወሬ አናፋሾች በተለያዩ ሩሞች ሲያወሩ ነበር ፣ ግን በምን ማስረጃ ? ሰው በመኪና ገጭቶ
ገድሏል ተብሎ ፍርድ ቤት ቀርቦ የተወሰነበት ቴዲ ፣ ሽራተን እንዲደሰት የሚያደርገው ማነው ? ወያኔ ? ምክን
ያት ? ይህስ ቢሆን ምን ስሜት የሚሰጥ ወሬ ሆነና ተናፈሰ ? አይ ፓልቶክ !!!

ታስታውሱ እንደሆን ሁለቱን የፓልቶክ ቁንጮዎች ፣ ዲያስፖራንና ከረንት አፌርስን ሁለቱ የጥፋት መልዕክተኞች
ያቋቋሙት እንጂ በኢትዮጵያዊያን የተመሠረተ አይደለም ተብሎ ፣ ከመጀመሪያው የፓልቶክ ምሥረታ አንስቶ
ሲናፈስ የነበረውን ጉምጉምታና ፣ እንዲሁም በፓልቶኮቹ ውስጥ የተካሄደውን ትግል የማኮላሸት ፣ ሞራል የመግደል
ሁኔታዎችን እየገመገምን እዚህ ላይ ደርሰናል ። ዛሬስ ዕውነቱ ይውጣ ቢባል ምን ያስፈራል ? ዕውን ባለቤቶቹ
ወይም ንጉሦቹ ኢትዮጵያዊያን ናቸው ? ወይስ ሌላ ? በተሰኙ ጥያቄዎች ዙሪያ ኢትዮጵያዊያን ተወያይተው
አንድ እልባት ላይ ካልተደረሰ በቀር ፣ በፓልቶኮች ውስጥ የሚካሄደው ውዥንብር የኢትዮጵያን የነፃነት ትግል
አሁን ካለንበት የባሰ ይጎዳዋል ብዬ አስባለሁ ። ካለፈው ሁኔታ እንዳየነው ከረንት አፌርስና ዲያስፖራ አንዱ ሌላ
ውን በነገር ይጠልፍ የነበረበት ጊዜ ባያከትምም ፣ ጥቂት ቀዝቀዝ ያለው ግን ዲያስፖራ በከረንት አፌርስ ተዘርሮ
ነው ። በሌላም በኩል በሁለቱ ተቧዳኞች አሸናፊነትና ተሸናፊነት አንፃር የማስመሰል ባኅሪያትም አይታጣባቸ
ውም የሚል የበርካታ ታዳሚዎች ግምት መኖሩም አያከራክርም ። ለማንኛውም ጠረባው ፣ ሾኬው የታዳሚ
ዎችን የመናገር መብት አፈና በነዚህ በሁለቱ ቁንጮዎች ብቻ ሳይሆን ፣ በሁሉም ፓልቶኮች እንዳለ ነው ።

ያለፈን ትዝታ ማስታወስ ብንሞክር ፣ በከረንት አፌርስ ውስጥ ብዙ ታዋቂ ሰዎች ተበራክተው ነበር ፣ ከጋዜ
ጠኛው ፣ ከታሪክ አዋቂው ፣ ከደራስያን ፣ ከኪነቱ ባለሙያዎች ፣ የፖለቲካው ዕውቀት ካላቸው ፣ ከወታደራዊ ፣
ከአርበኞች ፣ ባጠቃላይ የተለያየ ሙያ ካላቸው ብዙ ቁምነገሮች ሲደመጡ ነበር ። እና አሁን የት ጠፉ ?ለምን
በተጀመረው ጥንካሬ አልተዘለቀም ? ተብሎ ቢጠየቅ ፣ መልሱ አሁን እየተካሄደ ያለው የጥቂት ንጉሦች ግሩፕ
ፈላጭ ቆራጭነቱን ስለገፉበት ነው ማለት ይቻላል የሚሉም ብዙዎች ናቸው ። በዚያም ላይ ባውንስና ሬድ ምል

*ክቶች ስለሚያስፈራሩ ፣ የበርካታ ተሳታፊዎች ሽሽት ተባብሷል ። ዛሬ ዛሬ ጥቂት አድሚኖች ከንጉሦቹ ጋር
ስላልተጣጣሙ ፣ ሪዛይን አድርገናል ባይሉም ሽሽት ጀምረዋል ። የብዙ አድሚኖች ሰበብ ሥራ በዛብን የሚል
ቢሆንም ፣ ውስጡ ሌላ ነው ። ከረንት አፌርስ ትላልቀ ሥራዎችን በመከወን በተሳታፊው ጥንካሬ ትግሉን ተወጥ
ቷል የተባለለትን ያህል ፣ አሁን አሁን እየፈጸማቸው ያሉ ተግባሮቹ የወያኔ ቱልቱላነት በግልጽ ነካክቶታል እያሰ
ኘው ነው ። እነዚያን በኢትዮጵያ ሕዝብ ደም የተጨማለቁትን ፣ ታምራት ላይኔንና እሰዬ አብርሃን እየጠቃቀሱ
ማውራት ፣ እንዲያውም ይብስ ብሎ እሰዬን በመጋበዝ ውይይት መካሄዱ በርካታ ኢትዮጵያዊያንን አሳዝኗል ።
ሩሙን አስጠርጥሯል ፣ ግምት ውስጥም አስገብቷል ፣ ቢባል ቃለ አጋኖ አይሆንም ። ለመሆኑ እሰዬ የተጋበ
ዘው ያለፈና በደም የተጨማለቀበትን ወንጀሉን ሲያሰማን እሰየው አበጀህ እንድንለው ነው ? ወይስ የወደፊቷን
ኢትዮጵያ ብሩኅ-ተስፋ ሊያመጣልን ይችላል ተብሎ ? ዕውን ኢትዮጵያችን ጀግናና አስተዋይ ልጆች አጣችና
ሀገራችንን ለመቃብር ያሰናዳውን ከዛዲ ተማጽነን ነፃ ሊያወጣን ? ወይስ ከዚህ ሰው የሚቀሰም ትምህርት
ስላለ ? ይህስ ድርጊት ማምታታት ወይስ ግንዛቤ ማጣት ? የበኩሌ መልስ ሁለቱም ይሆናል ምክንያቱም
1/ ወያኔ የጀመረው የኢትዮጵያን ሕዝብ የማምታታት ሁኔታ በአብዛኞቹ ፓልቶኮች የመካሄዱ ነገር እያደገ መም
ጣቱን ፣ 2/ ሩሙ በዕውነተኛ ኢትዮጵያዊያን የመመራቱ ነገር አጠራጣሪ ነው የሚባለውን ሐሜት ስላጎላውና ፣
ግንዛቤ የሚሉትን አመለካከት ሩሙ እንዳልተጠቀመበት ስለሚያሳይ ነው ። ለዚያውም አንዲት ታዳሚ እሰዬ
በተጋበዘበት ዕለት የተናገረችው ፣ ለከረንት ንጉሦች ዕቡይ ተግባራት ታላቀ ማስረጃ ነው ። የእንታችንን ኒክ ኔም
በዚህ ላይ መግለጽ አልፈልግም ነገር ግን ያለችውን ለአብነት እጠቀሳለሁ ። “ ይህ ሩም የኔ ሩም ነው ፣ ወገኖ
ቼን የጨፈጨፈውን በደም የተጨማለቀውን እሰዬ የምትሉትን ገዳይ ለላከብረውም ፣ እናንተ እንግዳችን ነው
እስከጠራነው ድረስ እናከብረው ብላችኋል !! ገዳይ ለምን አላከበረችም የምትሉ ከሆነ እኔ አላከብርም ! ብትፈ
ልጉ ከሩሙ ልታባርሩኝ ትችላላችሁ ። “ ብላለች ። በርግጥ ኢትዮጵያዊ ትግላችን የጠነከረ እየመሰለን ፣ ነገር
ግን በሌላ አቀጣጫ ውስጣችን እየተቦረቦረ መሆኑ ለሁላችንም ገና የተሰማን አይመስልም ። እሰዬም ይሁን
ታምራት በስመ እሥር ቤት በደንብ ሠልጥነው ፣ ቀደም ሲል አብርሃም ያየህ በወያኔያዊ ክህነት የተጫወተውን
የ „ dis-information „ ሚና ለመጫወት የመጡ ፣ የወያኔ ሽፋኖች መሆናቸው በአብዛኛው ኢትዮጵያዊያን
ዘንድ የታመነና ፣ ብዙም የተባለበት ነው ። ምናልባት እነሱ ብልጠታቸውን ሲያጎለብቱ የኛም ሞኝነት እያደገ
መምጣቱ ይሆን ? ለማንኛውም በአሁኑ ጊዜ በፓልቶኩ ውስጥ ቀራጥ እኅቶች ብቀ እያሉ ስለሆነ ፣ ሞራላቸውን
ይበልጥ ማጠናከር ይኖርብናል ። ማንኛችንም ብንሆን በደም ከተጨማለቁ ወንጀለኞች ጋር ውይይት አያስፈ
ልገንም ፣ የሚል ቆራጥ ውሳኔ ከላይ እንደጠቀስኳት እኅታችን ማሳለፍ የሚጠበቅብን ይመስለኛል ። አጥፊ
ኃይላት ተንኮላቸውን ሲያባብሱብን እኛም ሆድ እየባሰን በውስጣችን የታመቀውን ብሶት ማውጣት እንዳንችል
ከወያኔ ጀምሮ ሁሉም አደናጋሪ ከሆነብን ፣ መቼ ነው ከዚህ የፓልቶክ ውዥንብር ነፃ ሆነን ፣ በዚህ ሥልጡንና
ሁለገብ ሚዲያ የሰከነ ፖለቲካ በማካሄድ ሀገርና ሕዝባችንን ነፃ በማውጣት እንደሌላው ዓለም ተረጋግተን የምን
ኖረው ? ይህ ጥያቄ የሁላችን ሊሆን እንደሚገባው ሁሉ መልሱም ከያንዳንዳችን ይጠበቃል ።*

*እንዲያው በነገራችን ላይ ፣ እንዴት ሌላ መልካም የፓልቶክ ሩም አላስተዋልክም ? ሳትሉኝ እንደማትቀሩ
ይሰማኛል ! የዚህም ምላሽ ቀላል አይደለም ። በመልካሞቹ ውስጥ መጥፎ አመለካከት ያላቸው እንደመኖራ
ቸው ሁሉ ፥ መጥፎ አመለካከት ባላቸውም ውስጥ ጥሩዎቹ እንዳሉበት ነው ። በዘር ድርጅት ሩም ውስጥ
ስገባ ፣ አንዱ ኢትዮጵያዊነት ነው የሚያዋጣን ፣ ሲል ሌላው በዘር ህመም ተለጉሞናቀናው መንገድ ጠፍቶበት
አስተውያለሁ ። በአምልኮተ-ሃይማኖት ሩም ውስጥ ስገባ ፣ አንዱ ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው ፣ እንደ
ቀድሞአችን ተከባብረን እንኑር ሲል ሌላው አክራሪ ሃይማኖተኛ ያከረረው እስኪበጠስለት ድረስ ያላዝናል ።
የፖለቲካ ድርጅቶች የፓልቶክ ሩም በግልጽ እንዳላቸው ባላውቅም ፣ በተለያዩ ሩሞች ይወደሳሉ ! በተለያዩ
ሩሞች ይረገማሉ ! እንዲያው በጥቅሉ ኢተፖድህ ፈረሰ ፣ ቀንጅት ተከፋፈለ ፣ አንዱ ሌላውን ዋጠው ፣ እነ
እገሌ አልተስማሙም ፣ እየተባለ ፣ ድርጅቶች ሲፈጠሩ ሲገነቡና ሲፈርሱ ፣ ከኃይለ ሥላሴ በኋላ የ36
ዓመታት ጊዜ በከንቱ አቃጥለናል ። በዚህም እንደ ሰው ማሰብ ተስኖን ይሆናል ብለን ማንነታችንን አልፈተሽ
ንም ። እንደምታውቁት በሰለጠነው ዓለም የሁሉ አገር ሕዝብ ፣ የሁሉ ዕምነት ፣ ጥቁር ነጭ ሳይል የሚኖርበት
ነው ። በመሠረቱ ሰው በሰውነቱ እንጂ ፣ ክብርና ውርደቱ በዘርና ዕምነቱ አይመዘንም ። ከማንም ይፈጠር ፣
ከየትም ይምጣ ፣ ሃይማኖት ይኑረው አይኑረው ጥያቄ የለበትም ። ለዚያም ነው የአውሮፓዎቹ መንግሥታት
ዛሬ በአንድ ቤት ጣራ ሥር መኖር የቻሉት ። እኛ ግን በአንዲት ሀገር ተፈጥረን አብረን አድገን ፣ ሃዘን ደስታ
ችንን ተጋርተን ፣ የመጣውን ጠላት ሁሉ አንድ ሆነን መክተን ፣ በዚህም ማንነታችንን በዓለም ላይ አሳውቀን ፣
አሁን ያለንበት ሁኔታ የማያሳፍረን ከሆነ ፣ እንደ ሰው የማሰቡ ነገር ገና ይቀረናል ማለት ነው ። በርግጥ የኛን
ሕዝብ እየተጫወቱበት ያሉት ፣ የዘርና ሃይማኖት ባላንጣነትን የተከሉበት ፊታውራሪዎቹ ናቸው ብል አያሳ
ፍረኝም ። ስለዚህ መልካም ነገሮችን ለማግኘት ደካማ ጎኖችን ማስወገድ ብቻ ነው ጥሩ መስሎ የሚታየኝ ፣
ያንንም ለማድረግ ኢትዮጵያዊያን ሐቀን ሙጥኝ ማለት ይጠበቅብናል ። በሀገር ጉዳይ ላይ አንድ-ወጥ የሆነ
የዓላማ ጽናት ያስፈልገናል ። በፓልቶኩም በኩል ኢትዮጵያዊ ራዕይ ያላቸው ሩሞች መፈጠር አለባቸው ።
በወጣቱ በኩል ወጣቱን በትክክል ያቀፈ ፣ በአዛውንቶችም በኩል እንዲሁ ፣ በሴቶችም በኩል የተጠናከሩ ኢት
ዮጵያዊነትን በትክክል የሚያንጸባርቁ ፣ በአርበኞችም በኩል ካለፈው ስህተት ትምህርት የወሰደ ጠንካራ ኃይል
እንዲመሠረት የሚያስችሉ ሩሞች መከፈት ይኖርባቸዋል ። በርግጥ እስካሁን ያረካኝ ነገር የለም ላለማለት ፣*
“ International Ethiopian womens org. forum „ *ሩሞች ውስጥ ብዙ ቁምነገሮች አድምጫለሁ ፣ መከ
ባበር ፣ ሥነ ሥርዓት የሰፈነበት ነው ፣ ውይይታቸው በሴቶች ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን ፣ ባጠቃላይ የሰብዓዊ
መብት ረገጣንና ፣ ጭቆናን ለማስወገድ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ጥሩ ሃሳቦችን በማቅረብ ነው ሲወያዩ ያጋ
ጠመኝ ። ዕውነት ለመናገር ይህ ሩም ጠንካራ ሴቶች እኅቶቻችን ያሉበትና ፣ ከወንዶች የላቀ ሥራ እየከወኑ
ያሉ መሆናቸውን ነው በተለያየ ጊዜ ገብቼ ያረጋገጥሁት ። ግን አንድቀን አንዷ ስትናገር “ ይህ ሩም የሴቶች*

*ነው ፤ ወንዶች አታስቸግሩን !! “ የማለት ሃሳብ አቀርባ አንዱን ተናጋሪ ስታስጨንቀው አድምጩ ተደነቅሁ ፤
ምናልባት ቀልድ ደባልቃ ይሆናል አላውቅም :: ለማንኛውም ያለ ሴት ተሳትፎ ወንዶች ለድል አይበቁም !!
እንደሚባለው ፤ ያለወንድ ተሳትፎ ሴቶች ለድል የሚበቁበት አጋጣሚ አይኖርምና ፤ ተባብረን ኢትዮጵያን
እናድን እያልሁ ፤ በጥቅሉ ግን ከላይ የገለጽሁት ሩም ውስጥ ጥሩ አመለካከት ነው ያለው !! መልካሞች
ናቸው ! በዚሁ ሊዘልቁበትና ፤ ሌሎቹም ሩሞች ፈለጋቸውን ሊከተሉ ይገባል :: አንዳንድ ሩሞች ለምሳሌ
እንደ የኢትዮጵያ አንበሶች ክለብ ፤ እንደ ልሣነ ኢትዮጵያ ፤ ጠንከር ያለም ባይሆን በአብዛኛው ኢትዮጵያ
ዊነት በትክክል የሚነገርባቸው ሩሞች ናቸው :: ጥቂት በሳል ሰዎችም ሲናገሩ አድምጫለሁ :: ነገር ግን
ልሣነ ኢትዮጵያ ሩም እንደ መስቀል ወፍ ብቅ እልም ከማለቱም በላይ አሁንማ በጭራሽ አይታይም ፤ እንጂ
አካሄዱ መልካም ነበር ከወያኔ ጋር የጀመርነውን ትግል በጥንካሬ ለመወጣት ጥርት ባለ መልኩ ኢትዮጵያ
ዊነትን የተላበሰ የፓልቶክ ሩም ከሌለ በቀር አሁን እየታየ ያለው በአብዛኛው ውዥንብር ለበስ በመሆኑ ፤
“ፓልቶክን ማመን ቀብሮ ነው “ የሚል ደረጃ ላይ አልደረስንም ማለት አይቻልም :: በሌላ መልኩም የወ
ያኔ ማንነት በኢትዮጵያዊያን ዘንድ የታወቀ በመሆኑ ፤ ወያኔ ኢትዮጵያ መቃብር እስክትገባ ድረስ የሚታገል
አጥፊ ኃይል ነው :: አሁን ለኛ የሚጠቅመን ወያኔ ከዚያች ምድረ ገጽ የሚጠፋበትን ተግባራት ሥራ ላይ
ለማዋል መከወን እንጂ ፤ ወያኔን መስደብ መውቀሱ ወይም መርገሙ ከሥልጣኑ ውንብድናው ፈቀቅ
የሚያደርገው ባለመሆኑ ይህን መገንዘብ ለምን ከባድ ይሆንብናል ? ይህንን ስል ወያኔን በመርገምና በመስ
ደብ ፤ የትግል ጊዜያችንን አናቃጥል ለማለት ነው ሃሳቤ ! ስለዚህም እነዚህ ሩሞች የተግባራዊ ሥራዎች መፍ
ለቂያ ቢሆኑ ዕድገት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ የሚል ዕምነት አለኝ ::* “ ethio opinion factory group “ *ማኅ
በራዊ ጉዳይን ብቻ በመመልከት ነፃ ሃሳብን የመግለጽ አዝማሚያ የሚታይበት ይመስላል ፤ ዳሩ ግን ከፖለ
ቲካው ነፃ የሆነ ማኅበራዊ ጉዳይ ግማሽ ጎኑ በድን ነው :: ከስድብ ልውውጥ ጥቂት የነፃ በመሆኑ ነው እንጂ
አካሄዱ ከኢትዮ ላቭ የሚለይ አይደለም :: ብዙ ቀልድም ስለሚበዛው ሊታረም ከቻለ መልካም ነው ::*

*በኔ ግምት በውጭው ሀገር ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ይኖረናል ፤ ብዙዎች የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምን
ይመስላል ? አሁንስ ሀገራችን እንዴት ናት ? እንደተሰደድንና እንደተሰቃየን ነው ወይ የምንኖረው ? እንደ ሰው
አስበንና በዜግነታችን ኮርተን የምንኖረውስ መቼ ነው ? ወዘተ....በሚል መጨነቁና ስሜቱን የሚገልጽበት ዕው
ነተኛ መድረክ መፈለጉ ሐቅ ነው :: ብዙ ጊዜ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ባይገኝም ፤ ምላሹ የሚገኘው የመወያያ
መድረኩ ሲኖር መሆኑን ጠንቀቆ ያውቃል :: ፓልቶክ የሚዲያ ሥራ ከሚገለጽባቸው የዘመናችን የመወያያ
መድረኮች አንዱ ቢሆንም ፤ በየሩሞቹ የሚደመጠው የሥርዓት-አልበኞች ወሬና ፤ የወያኔው ባዶ ቱልቱላ
ሊታደሙ የሚፈልጉትን ወገኖች ከሩቁ እያሸሸ ነው :: አንድ ወቅት የፓልቶክን ነገር አንስተን ከአንድ ጓደኛዬ
ጋር ስናወራ ፤ “ ፓልቶክን ከመሸታ ቤት ለይቼ አላየውም ! መሸታ ቤት ሰው የፈለገውን የሚሆንበት ፤ ቁም
ነገር የማይጨበጥበት ፤ በመጨረሻም በጸብ የምትለያይበት ነው !! “ ብሎኛል :: እርግጠኛ ነኝ በርካታ ታዳ
ሚዎች የትኛው መሸታ ቤት ነው ጥሩው ? ብሎ እንደሚያማርጠው ጠጪ ሩሞቹን ሲዞሩ እንደሚውሉና ፤
እንደሚያመሹ አልጠራጠርም :: በድፍረት አንዱ ሩም ውስጥ ዘው ተብሎ ቢገባም “ ለይተው ላላወቁት
ሰው የሌለውን ስም እየሰጡት ፤ በቀይ ካርድ እያባረሩትና ፤ በርካታ ኢትዮጵያዊያን የመወያያ መድረክ
እንደተነፈጋቸው ልናምን ይገባል :: ይህም ንፍገት ያለምንም ማጋነን ወያኔያዊ እንጂ ኢትዮጵያዊ ባኅሪ እንዳል
ሆነ ይሰማኛል :: አድሚኖቹ ቀይ ስለሰጡና ባውንስ ስላደረጉ ሰላማዊውን ኢትዮጵያዊ ወያኔ ነህ ስላሉም
እነርሱ ጤናማ ኢትዮጵያዊ ናቸው ማለት አይደለም ፤ እንዲያውም ትልቁ ችግር ያለው ከነርሱ ዘንድ ነው::*

*እንግዲህ የጀመርሁትን ለመቋጨት ያህል ፤ የፓልቶኮችን ውይይትና ነገሮችን በጥቅል እንደ ምናየው ብዙ
ደካማ ጎኖች አሉብን ፤ ውዥንብሮቹ እየጨመሩ ነው ፤ በበኩሌ ወጣቱ ትውልድ ጊዜ የጣለበትን አደራ ለመወ
ጣት ቆራጥ ሆኖ በመነሳት የተስተካከለ አቀጣጫ ሊከተል ይገባዋል :: ውዥንብር ፈጣሪዎችንም ጠንክሮ መፋለ
ምና ከመድረክ ውጭ ሊያደርጋቸው ይገባል :: ያንን ካደረገ ብቻ ነው ሽማግሌዎች ይብቃችሁ ልጆችሁ ደርሻ
ለሁ አርፋችሁ ተቀመጡ !! ብሎ መናገር የሚችለው :: ያለበለዚያ ግን ሽማግሌዎቹም ሀገሩን የማያኮራ ፤
በጉራ የተወጠረና ፍሬ አልባ የሆነ ልጃቸውን ሊያደምጡት እንደማይፈልጉም ወጣቱ ሊሰማው ይገባል :: ያች
ሀገር የተጋደሉላትና ደስታ-ሃዘንን ያሳለፉባት ፤ ሲሞቱ የሚቀበሩባት በመሆኗ ፤ አሁንም ነፃነትን ሊያጎናጽፏት
ይጥራሉ እንጂ የግርግር ፈጣሪዎችን ድንፋታ ፈርተው ወደኋላ የሚሉ አይመስለኝም ::*

*□□□የፓልቶኩ ግርግር ሊያከትም የሚችለው ከፍ ብሎ በገለጽኋቸው መልክ ይሆናል ብዬ አስባለሁ ! በተረፈ በዕ
ድሜ ጸጋ ኖረው በሕይወት ልምድ ውጣ-ውረዱን ያለፉ አባቶችና እናቶች ፤ የልጆቻቸውን የሕይወት አቀጣጫ
ለማስተካከል ኃላፊነቱ ስላለባቸው ከወጣቱ ትውልድ ጎን በጥንካሬ በመቆም ፤ ወጣቱም ሰውን ከመዘርጠጥ ባኅ
ሪው ፍጹም ነፃ ሆኖ ዘመናዊውን ፖለቲካ በሰከነ መልኩ በማራመድ ፤ ሀገራችን ከገባችበት መቀ ልናወጣት
ይገባል :: ፓልቶክን ለወሬ ሱስ መወጫ ከማድረግ ይልቅ ቁምነገር እንሥራበት እላለሁ !! አመሰግናለሁ*

*መልካም ውይይት በያላችሁበት*

*መለኮት ባዩህ*